**Tigray Diaspora Inter-Religious Council (TDIRC)**

**ትግራይ ዳያስፖራ ናይ ሃይማኖት ትካላት ጉባኤ (ትዳሃትጉ)**

# <u>አስቸኳይ የሕይወት አድን ጥሪ!</u>

ለኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ አ.አ
ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን
ለኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላላ ምክር ቤት
ለኢትዮጵያ ወንጌላዉያን አብያተ-ክርስትያናት ሕብረት
ለኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ-ክርስቲያን
ለኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ-ክርሰቲያናት ካውንስል
ለኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች፣ ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ፣ ሐገር ሽማግሌዎች፣ የሚድያ አክቲቪስቶች
እንዲሁም ለአዲስ አበባ፣ ለባሕርዳር፣ ለጎንደር፣ ናዝሬት እና ሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ነዋሪዎች በሙሉ።

የትግራይ ሕዝብ ላለፉት አራት ዓመታት በቃላት ለመግለፅ የሚከብዱ ዘግናኝ ግፎች ሲፈፀምበት መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በተለይ ደግሞ ካለፈው አንድ ዓመት ጀምሮ የባዕድ ሠራዊት ጭምር በማስገባት መጠነ ሰፊና አውዳሚ ጦርነት ተከፍቶበት የብዙ ሺዎች ንፁሐን ሕይወት ጠፍቷል፣ ብዙ ሺ ሴቶች በግፍ ተደፍረዋል፣ ሀብትና ንብረቱ ተዘርፎና ወድሞ ለከፋ ድህነት ተጋልጠዋል፣ ከሌላ ዓለም ተለይቶ የምግብና የመድኃኒት እርዳታ እንዳያገኝ ተከልክሏል፣ ከተሞች በአየር ተደብድቧል ወ.ዘ.ተ።

ይህ አልበቃ ብሎ አሁን ደግሞ ከትግራይ ውጭ ባሉት የኢትዮጵያ ከተሞችና መንደሮች የሚኖሩ ንፁሐን የትግራይ ተወላጆች በማንነታቸውና በቋንቋቸው ብቻ ተለይተው እየታሰሩ፣ እየተገደሉ፣ ንብረታቸው እየተዘረፈ በአስቃቂ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ይባስ ብሎም ይህ የተጀመረው ጀኖሳይድ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና አድማሱን እንዲያሰፋ ከተለያዩ ሚዲያዎችና የሕብረተሰብ ክፍሎች በግልፅ የእልቂት ጥሪ እየተላለፈና እየተሰበከ ይገኛል፡፡

በመሆኑም ከላይ የተዘረዘራችሁ የሃይማኖት ተቋማትና የኅብረተሰብ ክፍሎች የተሸከማችሁትን ታሪካዊ ኃላፊነትና የሞራል ግዴታችሁን ተጠቅማችሁ ይህ በትግራይ ተወላጆች ላይ የታወጀውን የዘር ማጥፋት ጥሪና ድርጊት በአስቸኳይ እንድታወግዙ፣ እንድታስቆሙና ለትግራይ ሕዝብ ከለላ እንድትሆኑት በታላቅ ትህትና እንማፀናለን።

ፈጣሪ ሰላሙን ይሰጠን!

ትግራይ ዳያስፖራ ናይ ሃይማኖት ትካላት ጉባኤ (ትዳሃትጉ)
(ከኦርቶዶክስ፣ እስልምና፣ ካቶሊካዉያን ፣ እና ወንጌላዉያን ተወካዮች)
ዋሽንግተን ዲሲ
ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ/ም

Tigray Diaspora Inter-Religious Council (TDIRC)
501(c)(3) NON PROFIT
SEAL
CORPORATION
District of Columbia

**2730 22nd St NW, Washington, DC 20118; Tele: +1202 503 9168; +1510 439 7406**

**The Golden Rule: "Treat Others The Way YOU Want To Be Treated**